# አንድ የቅንጅት አባል ፍትሕ ማጣታቸውን ገለጡ

አቶ አሸቱ ከበደ ሸንቁጥ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባል ንብረታቸውን በሥርዓተ-አገዛዙ ካድሬዎችና በግብረ አበሮቻቸው ተዘርፈው እስከ ዛሬ በሕግ አግባብ ተገቢውን ፍትሕ ያላገኙ መሆናቸውን ሰሞኑን ገለጡ።

ቀደም ሲል በአርሲ ዞን በደደታ ወረዳ በዴራ ከተማ በ01 ቀበሌ ነዋሪ የነበሩትና ባሁኑ ጊዜ ተባርረው በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙት አቶ አሸቱ ንብረታቸውን የተዘረፉት ሚያዝያ 4 ቀን 1998ዓ.ም ከሌሊቱ በ8 ሰዓት ላይ እንደነበር አስረድተው ከዚያን ጊዜ አንስቶ ለሥርዓተ-አገዛዙ የሕግ አካላት በተከታታይ ቢያመለክቱም ለጉዳያቸው ትኩረት የሚሰጥ አካል ማጣታቸውን በምሬት ተናግረዋል።

በነበሩበት በዴራ ከተማ አራት ጊዜ ታሥረው የተፈቱ ከመሆናቸውም በላይ በቀን ሁለት ጊዜ ወደ ተዘጋጀላቸው ሥፍራ እየቀረቡ እንዲፈርሙ ይገደዱ እንደነበር የተናገሩት አቶ አሸቱ ቤተሰባቸውም ተበትኖ በከፍተኛ ችግር ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

በጠቅላላው ከብር አሥር ሺህ በላይ ዋጋ የሚያወጣ ንብረት የተዘረፉ መሆናቸውን የገለፁት አቶ አሸቱ በመጨረሻም የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶችና የሚመለከታቸው አካላት በግፍ የተዘረፈው ንብረታቸው እንዲመለስላቸው የበኩላቸውን ግፊት ሁሉ እንዲያደርጉ አበክረው ጠይቀዋል።

EthioLion.Com